# ዶክተር ዜሮ

ልደቱ በጋሻው የኛው ድ/ር ዜሮ
እያደሩ ጥጃ ከንቱ ተመክሮ
አወይ አለመማር ወይ አለመታደል
ስንቴ ሰው ይሞታል እየገባ ገደል?

ማስተዋል ለሚችል አርቆ ለማየት
ዕድሜም ትምህረት ነው እንደ ቀለም እውቀት
ለዶ/ር ዜሮ ግን የኦነግ አብነት
አልታይህ ያለው የመገንጠል ዕምነት
እንደ ብርሃኑ የፈረንጅ ቅጥረኛ
እንዳይሆን ጠርጥሩ የጅሮ ቀበኛ!

............

## ሳቂ ወይም አልቅሽ

እንዳትስቂ ደስታ የነሳሽን ሀዘን
መለኪያ ፈልገሽ በህሊናሽ ማዕዘን
መሆንሽን አውቀሽ የሙት ባልደረባ
ልሳቅ ታልሽ ሳቂ ወይ ታጠቢ በዕምባ።

ሀዘንተኛ ሆነሽ የሞተ-በቁሙ
ተልከስክሶ እሚታይ ሰውነትሽ አፅሙ
እያለሽ የሌለሽ ሰው ሆነሽልና
ሳቂ ወይም አልቅሽ በህዝብሽ ገመና።

አገር በቀል ጠላት የውጭ ሰው ጠርቶ
መቆሚያ መሄጃ መራመጃ ነስቶ
መሬቱ አይደለም ወይ ያስወገደሽ ተፍቶ?

ስለዚህ እህቴ ልጅሽን ስትድሪ
ለማጫ ያሰብሽው የመሬት ዕዳሪ
ይታደልሽ እንደሁ ተስፋሽን ሰንቀሽ
ለጌታ አደሪና አንቺም እንደ ህዝብሽ
ሳቂ እንደማሽላ እያረረ ውስጥሽ!!

ሰኔ 2003
ለለምለም ፀጋው ግጥም መልስ

አብርሃም በየነ

EthioLion.Com